## ሱሑር እንዴት ተግባራዊ ይሆናል?

የፆም ማሰሪያ ምግብ (ሱሑር) ጥቂትም ሆነ በርካታ ምግብ በመውሰድ ተግባራዊ ይሆናል።አንድ ጉንጭ ውሃ መጠጣት እንኳ ከ«ሱሑር» ይቆጠራል።

አቡ ሰዒድ አል–ኹድሪይ እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

فعن أبى سعيد الخدري رضي الله عنه: ((السحور بركة، فلا تدعوه ولو أن يجرع أحدهم جرعة ماء، فإن الله وملائكته يصلون على المتسحرين)) رواه أحمد.

«የሌሊት ምግብ (ሱሑር) ረድዔት አለው። ስለዚህ አትዘንጉት። አንዳችሁ አንድ ጉንጭ ውሃ እንኳ ይጉንጭ። አላህና መላእ ክቱ በሌሊት ተመጋቢዎች ላይ እዝነትን ያሰፍናሉ።»

(አህመድ ዘግበውታል)

## የሚፈጸምበት ጊዜ

የሱሑር (የጾም ማሰሪያ ምግብ) ከግማሽ ሌሊት ጀምሮ ጐህ እስኪቀድ ድረስ ሊወሰድ ይችላል።ጐህ ሊቀድ ከመቃረቡ በፊት መሆኑ (ማዘግየቱ) ይበልጥ ተወዳጅነት አለው።

ዘይድ ኢብን ሳቢት (ረ.ዐ) እንዳወሩት:- «ከአላህ መልዕክተኛ ጋር በሌሊት ተመገብን።ከዚያም ወደ (ሱብሂ) ሶላት አመራን።» «በመካከላ ቸው ምን ያህል ክፍተት ነበር?» የሚል ጥያቄ ቀረበ። «ሃምሳ አንቀጽ» አሉ።

(ቡኻሪይ የዘገቡት።)

ዐምር ኢብን መይሙን እንዳስታወቁት:-«የሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች (ማታ) ሲያፈጥሩ ከማንም ሰው ፈጥነው ሲሆን ፆም ሲያስሩ ደግሞ ዘግይተው ነበር።»

በይሐቅ ዘግቦታል።

## ጐህ መቅደድ ሲያጠራጥር

ጐህ በመቅደዱ ላይ ጥርጣሬ ያደረበት ሰው መብላትና መጠጣት ይችላል– ጐህ መቅደዱን እስኪያረጋግጥ ድረስ። ምክንያቱም ጥርጣሬ ተግባርን ማገድ ስለማይኖርበት ነው። አላህ (ሱ.ወ) በቁርኣን የገለጸውም ይህንኑ ነው። መመገብ መቅደም ያለበት በእርግጠኝነት እንጂ በጥርጣሬ አይደለም።

﴿وكلوا واشربوا حتى يتبين لكم الخيط الأبيض من الخيط الأسود من الفجر﴾

«ከጎህ የኾነው ነጩ ክርም ከጥቁሩ ክር (ከሌሊት ጨለማ) ለናንተ እስከሚገለጽላችሁ ድረስ ብሉ! ጠጡም! ..» (አል–በቀራህ፥ 187)

አንድ ግለሰብ ለኢብን ዐብባስ (ረ.ዐ) እንዲህ አላቸው:- «እኔ (ሌሊት) እመገባለሁ–በተጠራጠርኩ ጊዜ ግን አቆማለሁ።» እርሳቸውም:- «ወደጥርጣሬ እስከማያደርስህ ወቅት ድረስ ተመገብ–ጥርጣሬ ውስጥ እንዳትወድቅ» አሉት።

አቡ ዳውድ እንዳጸፉት ፥አቡ ዐብደላህ (አህመድ ኢብን ሀንበል) እንዲህ ብለዋል:-«ጐህ በመቅደዱ ጉዳይ ላይ ጥርጣሬ ያደረበት መውጣቱን እስኪያረጋግጥ ድረስ ይመገብ።» ኢብን ዐብባስ፣ ዐጥጧ እና አውዛዒይም ተመሳሳይ አቋም አላቸው። ነወዊይ እንደጻፉትም የሻፊዒይ መዝሀብ ምሁራን ጐህ መቅደዱን የተጠራጠረ ሰው መመገብ የሚፈቀድለት መሆኑን ተስማምተዋል።

## 2) በፍጥነት ፆም መግታት (ማፍጠር)

ፆመኞች ፀሐይ ከጠለቀ በኋላ በፍጥነት ፆማቸውን መግታት ይኖርባቸዋል።

ሰህል ኢብን ሰዒድ (ረ.ዐ) እንዳወሩት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

((لايزال الناس بخير، ماعجّلوا الفطر)) رواه البخاري ومسلم

«ሰዎች ከበጐ ምግባር አይወገዱም–ፆም መግታትን (ማፍጠርን) እስካፈጠኑ ድረስ።»

(ቡኻሪይና ሙስሊም ዘግበውታል።)

በአንድ ወይም በሦስት...ተምር ማፍጠሩ ይወደዳል። ተምር ካልተገኘ ግን በውሃ ማፍጠር ይቻላል።

አነስ (ረ.ዐ) እንዳወሩት፥«የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በእሸት ተምር ያፈጥሩ ነበር—ከመስገዳቸው በፊት።ይህን ካላገኙ በደረቅ ተምር፤ ይህንንም ማግኘት ካልቻሉ ውሃ ይጉነጩ ነበር።»

(አቡዳውድና ሐኪም ዘግበውታል)

ሰልማን ኢብን ዓሚር (ረ.ዐ) እንዳወሩት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

وعن سلمان بن عامر: أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: (( إذا كان أحدكم صائما، فليفطر على التمر، فإن لم يجد التمر فعلى الماء، فإن الماء طهور)) رواه أحمد والترمذى.

«አንድ ሰው ፆመኛ ከሆነ በአንድ ተምር ያፍጥር፤ ተምር ካላገኘ ደግሞ በውሃ ያፍጥር፤ ውሃ የሚያጠራ ነውና።»

(አህመድና ቲርሙዚ ዘግበውታል።)

አነስ (ረ.ዐ) እንዳወሩት፥ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

قال أنس: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: ((إذا قدم العشاء فابدءوا به قبل صلاة المغرب ولا تعجلوا عن عشائكم)) رواه الشيخان.

«ምግብ (ራት) ከቀረበ የመግሪብ ሶላትን ከመስገዳችሁ በፊት ተመገቡ። (ሶላቱን) ከራት አታስቀድሙ።»

(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።)

ከላይ ከተጠቀሰው ሐዲስ እንደምንገዘነበው ከመግሪብ በፊት ማፍጠር ተወዳጅነት አለው። ምግብ ከቀረበ በኋላ ወደ ሶላት መቅረብ አግባብ አይደለም።

## 3) በማፍጠሪያ ወቅት የሚደረግ ፀሎት

ኢብን ማጀህ ዐብዱሏህ ኢብን ዐምርና ኢብን ዓስን በመጥቀስ እንዳ ወሩት ÷ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: ((إن للصائم عند فطره دعوة ماترد)) وكان عبد الله إذا أفطر يقول: ((اللهم إني أسألك - برحمتك التى وسعت كل شيء - أن تغفر لى))

«አንድ ፆመኛ በሚያፈጥር በት ወቅት የሚያደርገው ፀሎት ተቀባ ይነት አለው።» ዐብደሏህም በሚያ ፈጥሩበት ወቅት—«አላህ ሆይ! እኔ ሁለገብ በሆነው እዝነትህ ትምረኝ ዘንድ እማፀንሀለሁ» ይሉ ነበር።

የአላህ መልዕክተኛም «ጥማችን ተወገደ÷ ሕዋሳታችን ተጠናከረ÷ የአላህ ፈቃድ ከሆነም ምንዳችን ተረጋገጠ።» ይሉ ነበር—ሲያፈጥሩ። እንዲሁም:- «አሏሁምመ ለከ ሱምቱ ወዐላ ሪዝቂከ አፍጠርቱ። (ማለትም አላህ ሆይ! ለአንተ ፆሜአለሁ።አንተ በሰጠኸኝ ሲሳይም ፆሜን አቁሜአለሁ (አፍጥሬ አለሁ)» ይሉ ነበር።

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

وروى الترمذي بسند حسن أنه صلى الله عليه وسلم قال: ((ثلاثة لاترد دعوته: الصائم حتى يفطر، والإمام العادل، والمظلوم))

«ሦስት ሰዎች ፀሎታቸው አይመለስም—ፆመኛ እስኪያፈጥር ድረስ፤ ፍትሀዊ መሪ እና የተበደለ ግለሰብ።»

## 4) ፆምን ከሚፃረሩ ጉዳዮች ነፃ መሆን

ፆም ወደ አላህ ከሚያቀርቡ አንኳር ዒባዳዎች አንዱ ነው። አላህ (ሱ.ወ) ፆምን የደነገገው እያንዳንዱ ፆመኛ በሥነ-ምግባር የመጠቀና ለፈጠረው ጌታ ታማኝ ሎሌ እንዲሆን ለማስቻል ነው። በመሆኑም ጿሚው ግለሰብ የፆሙን መሠረታዊ ዓላማ ከሚያደናቅፉ ፀያፍ ተግባራት ሁሉ ነፃ መሆን መቻል አለበት። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿يا أيها الذين آمنوا كتب عليكم الصيام كما كتب على الذين من قبلكم لعلكم تتقون﴾

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ፥በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነገገ)! ልትጥነቀቁ ይከጀላልና።» (አል–በቀራህ፥ 183)

ፆም ከመብላትና ከመጠጣት መታቀብ ብቻ አይደለም። ከሌሎችም አላህ (ሱ.ወ) ከከለከላቸው ነገሮች መራቅ ያስፈልጋል።

አቡሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳወሩት፥ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

((ليس الصيام من الأكل والشرب، إنما الصيام من اللغو، والرفث، فإن سابك أحد، أو جهل عليك، فقل إني صائم إني صائم))

«ፆም ከመብላትና ከመጠጣት መታቀብ ብቻ አይደለም። ከከ ንቱ ንግግሮችና ረብሻ መጾምም ያስፈልጋል።አንድ ሰው ቢሰድብህ ወይም ቢተናኮልህ ‹እኔ ፆመኛ ነኝ፥ እኔ ፆመኛ ነኝ› በል።»

(ኢብን ኹዘይማ፣ ኢብን ሂብባንና ሐኪም የዘገቡት።)

ሙስሊም ሲቀሩ ሌሎች የሐዲስ ዘጋቢዎች እንዳወሩት፥አቡሁረይራ (ረ.ዐ) ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸውን ገልጸዋል:-

((من لم يدع قول الزور والعمل به فليس لله حاجة في أن يدع طعامه وشرابه))

«አስከፊ ንግግርን እና ተግባራትን ያልተወ ሰው ከምግብና ከመጠጥ መታቀቡ ብቻ አላህ ዘንድ ከቁም ነገር የሚገባ አይደለም። (አላህ ፆሙን አይቀበለውም።)»

አሁንም ከአቡ ሁረይራ እንደተወራው መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ):-

((ربَّ صائم ليس له من صيامه إلا الجوع، وربَّ قائم ليس له من قيامه إلا السهر)) رواه النسائي وابن ماجة والحاكم.

«በርካታ ፆመኞች አሉ፥ከፆማቸው ረሃብ እንጂ ሌላ የማያተርፉ፤ በር ካታ ሰጋጆችም አሉ–ከረጅም ሶላታቸው ድካም እንጂ ሌላ የማይ ጠቀሙ» ብለዋል።

(ነሳኢይ፣ኢብን ማጀህና ሃኪም የዘገቡት።)

## 5) ሲዋክ (መፋቂያ)

ፆመኛ ሰው በማንኛውም ወቅት ጥርሱን መፋቅ ይኖርበታል። ጧትም ሆነ ከሰዓት በኋላ ጥርስን መፋቅ የተወደደ ተግባር ነው።

ቲርሚዚይ እንደጻፉት÷ኢማሙ ሻፊዒይ ጧትም ሆነ ከሰዓት በኋላ መፋ ቂያ መጠቀም ልዩነት እንደሌለው አስገንዝበዋል።ነቢዩ ሙሐመድም (ሶ.ዐ.ወ) ፆመኛ በሆኑበት ወቅት በማንኛውም ሰዓት ጥርሳቸውን ይፍቁ ነበር።

## 6) መለገስና ቁርአንን ማጥናት

ልግስናና ቁርአንን ማጥናት በማንኛውም ወቅት የተወደደ ነው። በረመዷን ወር ግን የበለጠ ተፈላጊነት አላቸው።

ቡኻሪይ (ረ.ዐ) ኢብን ዐብባስን ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ ቸር ነበሩ። በተለይ በረመዷን ጂብሪል ጋር በሚገናኙበት ወቅት–ለጋስነታቸው ከፍተኛ ይሆናል። ጂብሪል በረመዷን ወር በእያንዳንዱ ሌሊት ነቢዩ ዘንድ በመምጣት ቁርአንን ያናብባቸዋል።እርሳቸው የሸመደዱትን ያሰሙታል–እርሱ ያዳምጣል። በጥቅሉ ግን የአላህ መልዕክተኛ ከማንም የበለጠ ቸር ሰው ነበሩ።

# 7) ከረመዷን በመጨረሻው አሥር ቀን በዒባዳ መበርታት

ሀ) ቡኻሪና ሙስሊም አዒሻን በመጥቀስ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የረመዷን የመጨረሻው አሥር ሲገባ ሌሊቱን (በዒባዳ) ያነጉ ነበር፤ የቤተሰባቸውን አባላትም እንዲነቁ ያደርጋሉ–ትጥቃቸውንም ያጠብቁ ነበር።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ:- «ነቢዩ በሌላው ወቅት የማያደርጉትን ጥረት በመጨረሻው አሥር ቀን ያደርጉ ነበር።»

ለ) ቲርሚዚ እንደዘገቡትና ዓሊይ(ረ.ዐ) እንዳሉት፥ «የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ቤተሰባቸውን እንዲነቁ ያደርጉና ሽርጣቸውንም ያስሩ ነበር።»